# በአከራይ ባለ ንብረት እና በተከራይ ፍርድ ቤት ውስጥ ይግባኝ ስለማመልከት

ይህ የመረጃ ገፅ በአከራይ እና ተከራይ ፍርድ ቤት ጉዳዮች ይግባኝ ይገልጻል። መረጃ የሚፈልጉ ተከራይ ወይም አከራይ ወይም በፍርድ ቤት ወረቀቶቸን ለመጻፍ ወይም ፋይል ለማድረግ ወደ አከራይ ተከራይ መረጃ ማዕከል መሄድ ወይም ለዕርዳታ ወደ ሌላ የህግ ባለሙያ መሄድ ይችላሉ። ለህግ ዕርዳታ የት መሄድ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ መረጃ በዚህ የመረጃ ወረቀት መጨረሻ ይገኛል።

## ይግባኝ ምንድነው?

ዳኛው ከችሎት በፊት ስለ ጉዳዩዎ ውሳኔ እንዲያደርጉ ከፈለጉ የፍርድ ቤት የይግባኝ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ይግባኝ አንድ ዳኛ በእርሶ ጉዳይ ላይ አንድ ነገር እንዲያደርግ የመጠየቅ ሂደት ነው። ባለንብረቱ ወይም ተከራይ ይግባኝ ማመልከት ይችላል። ተከራዮች አንዳንዴ ጉዳዩ እንዲሰረዝ፣ ተከራዩ ላይ የተወሰነ መደበኛ ፍርድ እንዲቀር ወይም ተከራይ ዘግይቶ የመከላከያ ማዘዣውን እንዲያደርግ እንዲፈቅድ ለማስቻል ይግባኝ ይጠይቃሉ። ባለንብረቶች በተከራይ ላይ ፍርድ እንዲሰጥ አንዳንድ ጊዜ ይግባኝ ይጠይቃሉ፤ ለምሳሌ ተከራዩ የጥበቃ መከላከያ ክፍያ ካልፈፀሙ። አንድ ይግባኝ በፅሁፍ የቀረበ በቃለ-መሀላ ፊት ለፊት ከሚሰጡት የግለሰብ የምስክርነት ቃል የሆነን መግለጫ ሊያካትት ይችላል።

## አንድን ይግባኝ ለማስገባት ክፍያ አለ?

በአከራይ እና ተከራይ ፍርድ ቤት ለእያንዳንዱ የይግባኝ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ 10 $ ያስከፍላል። አቤቱታ ለማቅረብ ምናልባት የገንዘብ ችግር ቢኖርብህ አቤቱታህን “ያለ ቅድመ-ክፍያ በማመልከት መቀጠል ትችላለህ።“ አንድ ዳኛ የእናንተን ይግባኝ ይገመግምና ጥያቄዎን ለመፍቀድ እና ላለመፍቀድ ይወስናል። በጥያቄዎ መሰረት የአዎንታ መልስ ከተሰጥዎ ያለ ክፍያ የአቤቱታ ሰነዶችዎን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ።

## ይግባኝ የጠየቀው ግለሰብ ለሌላኛው ወገን ቅጂ መስጠት አለበት?

በፍርድ ቤት ውስጥ ይግባኝ ለማቅረብ በሚፈልጉበት ጊዜ በርስዎ ጉዳይ በሌላኛው በኩል ለአከራይ ወይም ተከራይ ቅጂውን መስጠት አለብዎ። በርስዎ ጉዳይ በሌላኛው በኩል ያለው ተከራይ ወይም አከራይ ጠበቃ ካለው ያቀረቡትን የይግባኝ ማመልከቻ ቅጂ ለጠበቃው የግድ መስጠት አለብዎ። ተከራዩ ወይም አከራዩ ጠበቃ ከሌለው ለተከራዩ ወይም ለአከራዩ በቀጥታ ቅጂውን መስጠት አለብዎ። የይግባኝ ማመልከቻዎን ግልባጭ በፖስታ በመላክ ወይም በቀጥታ በአካል መስጠት ይችላሉ።

## ዳኛው የእኔን ውሳኔ የሚወስኑት መቼ ነው?

አንድን ይግባኝ በሚያስገቡበት ጊዜ በዳኛው ፊት ቀርበው ጉዳዩ እንዲሰማሎት ወደ ፍርድ ቤት መሄድ አለብዎት። አብዛኛዎቹ የይግባኝ ጥያቄዎች ችሎት በ 10: 00 a.m. ይካሄዳሉ። ይግባኙ ከተመዘገበው ቀን ቢያንስ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ችሎቱ ላይ ይቀርባል። አንድን ይግባኝ እያቀረቡ ከሆነ፤ በጉዳይዎ ሌላኛው በኩል ላለው ለአከራይ ወይም ተከራይ መጥራት ወይም በሌላ በኩል ላለው ግለሰብ ጠበቃ በፍርድ ቤት ውስጥ ለመገኘት ምን ቀን እንደሚመቻቸው ለማወቅ ለመጠየቅ ሊፈልጉ ይችላሉ።

## የይግባኝ ማመልከቻ ደርሶኛል። ማድረግ የሚጠበቅብኝ ነገር አለ?

በርስዎ ጉዳይ ላይ ይግባኝ በሌላኛው አከራይ ወይም ተከራይ የይግባኝ ጥያቄ ከቀረበ እርስዎ ከፈለጉ መልስ በጽሁፍ መስጠት ይችላሉ። ለይግባኝ ጥያቄ የሚፃፍ ምላሽ “ተቃውሞ” ተብሎ ይጠራል። "ለማጠቃለያ ፍርድ የተጠየቀ ይግባኝ" ካልሆነ <u>በስተቀር</u> በአከራይ እና ተከራይ ፍርድ ቤት ውስጥ ለመሰማት ቀጠሮ ለተያዘለት ችሎት ላይ የተቃውሞ ምላሽ በፅሁፍ ለማስገባት አይጠበቅቦትም። ለ"ለማጠቃለያ ፍርድ የተጠየቀ ይግባኝ" ከደረስዎ የተቃውሞ ምላሽዎን የግድ ማስገባት ይኖርቦታል፤ ከዚያም ወዲያውኑ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ጠበቃ ማነጋገር አለብዎ።

ዳኛው በእርሶ በኩል ያለውን ሀሳብ እንዲያደምጡ የሚፈልጉ ከሆነ ወደ ፍርድ ችሎት መሄድ ይኖርቦታል። ወደ ፍርድ ቤት ችሎት ካልሄዱ፤ እርስዎ በቦታው ባለመገኘትዎ ብቻ የይግባኝ ጥያቄዎን ሊያጡ ይችላሉ።

በርስዎ ጉዳይ ላይ የችሎት ላይ ክርክር ካለበት የተወሰኑ ውሳኔዎች በተመደበው ዳኛ ውሳኔ የሚወሰኑ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በአከራይና ተከራይ ፍርድ ቤት ውስጥ ባለው ዳኛ ውሳኔ ይሰጣቸዋል። በተመደበው ዳኛ ውሳኔ ለሚያገኙ ማንኛውንም አይነት የይግባኝ ጥያቄ ተቃውሞዎን በጽሑፍ ማስፈር ይኖርብዎታል። እነኝህ አቤቱታዎች አብዛኛውን ጊዜ በችሎት እንዲታይ የታቀዱ አይደሉም፤ ስለሆነም የሆነ ነገር በጽሁፍ ማስገባቱ የይግባኝ ጥያቄው ለምን እንደማያስፈልግ መግለጫብቸኛ እድልዎ ይሆናል። የጽሑፍ ተቃውሞ ማቅረብ ያስፈልግዎ እንደሆነ እርግጠኛ ካልሆኑ ወዲያውኑ ለጠበቃ ያነጋግሩ።

## በፍርድ ችሎቱ ላይ ምን ይፈጠራል?

ጉዳዩ በሚሰማበት ወቅት ይግባኙን ያቀረበው ሰው ለምን ለፍርድ ቤቱ ለምን ይግባኙ መፈቀድ እንዳለበት እና ለክርክራቸው ድጋፍ ለመስጠት ማስረጃን ሊያቀርብ ይችላል። በሌላው በኩል ደግሞ አከራዩ ወይም ተከራዩ ጥያቄው ለምን ፍርድ ቤቱ ይግባኙ መፈቀድ <u>እንዳሌለበት</u> እና ለክርክራቸው ድጋፍ የሚያደርግ ማስረጃን ለማሳየት እድሉ ይኖራቸዋል። በአብዛኛው ጉዳዮች ላይ ዳኛው ለይግባኝ ጥያቄው ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ ውሳኔውን ይወስናል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ዳኛው ውሳኔ ለመወሰን ተጨማሪ ጊዜ ሊፈልጉ ይችላሉ እና እርስዎ ወይ ሌላ ችሎት ይኖርዎታል ወይም የፍርድ ውሳኔን (ወይም "ትዕዛዝ") ቅጂ በፖስታ ይላክልዎታል።